# ለአራተኛው በሰሜን አሜሪካ
# የካህናትና ምዕመናን ጠቅላላ ጉባዔ የቀረበ
# የሥራ ክንውን ዘገባ

ከሁሉም አስቀድሜ በሠላም በጤና እና በፍቅር ጠብቆ እዚህ ላደረሰን ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምሥጋና ይድረሰው እላለሁ።

የተከበራችሁ ካህናት፣ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን፣ እናቶች፣ አባቶች፣ ወንድሞችና እህቶች፤ እንደምን አደራችሁ?

በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ካህናትና ምዕመናን ጉባዔ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ አሁን ለአራተኛ ጊዜ እስከተገናኘንበት ወቅት ድረስ ያከናወናቸውን፣ ወደፊትም ልናደርጋቸው የሚገባቸውን አበይት ጉዳዮች ከዚህ በታች ባጭሩ እገልፃለሁ።

በጉባዔው በአባልነት የተመዘገቡና ሌሎችም በርካታ አብያተ ክርስቲያናት በሰሜን አሜሪካ እራሱን «ስደተኛው ሲኖዶስ» እያለ ከሚጠራው ወገን ጋርም ሆነ መንበሩ ኢትዮጵያ ከሆነው ሲኖዶስ ጋር በአስተዳደር ኅብረት ሳያደርጉ «ገለልተኛ» ተብለው በመጠራት ቤተክርስቲያንን በመመሥረትና በማሳደግ ላይ በማተኮር ብዙ አመታትን አሳልፈዋል።

እንደሚታወቀው ጥር 13 እና 20 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰሜን አሜሪካ፣ ዋሽንግተን ዲሲ እና በካናዳ ቶሮንቶ ላይ የተከናወነው የጳጳሳት ሹመት ሲሰማ ይህ ድርጊት አንድነቷን አጽንታ የቆየችውን ጥንታዊት ቤተክርስቲያን ለሁለት የሚከፍልና የሚያዳክም፣ እንዲሁም ቤተክርስቲያኒቱን ከበው ለሚገኙ ጠላቶች ጥቃት ለመፈጸም እድል የሚሰጥ መሆኑን በመገንዘብ፣ በአንጻሩም ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘው ሲኖዶስ ዘረኝነት፣ የአስተዳደር ድክመትና ጠቅላላ የአመራር ጉድለት ማሳየቱ ያሳዘናቸው ከ13 አብያተ ክርስቲያናት የተውጣጡ ካህናት በቴሌ-ኮንፈረንስ መወያየት ጀመሩ።

## የመጀመሪያው የካህናት ስብሰባ፤

እነዚሁ በቴሌፎን ሲገናኙ የነበሩ ካህናት በዋሽንግተን ዲሲ ርዕሰ-አድባራት ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ከየካቲት 30 እስከ መጋቢት 1 ቀን 1999 ዓ.ም. ተሰብስበው፡-

1. «ተሰደድኩ» የሚለው የጳጳሳት ቡድን ያደረገውን የጳጳሳት ሲመት «ኢቀኖናዊ ነው» በማለት የቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ያስተላለፈውን ውግዘት ደገፉ።

2. በአገራችን ያለው ቅዱስ ሲኖዶስም ቅሬታ የሚታይባቸውን የአስተዳደር ድክመቶች እንዲያሻሽልና ዘረኝነትም ሆነ ፖለቲን ከማንጸባረቅ እንዲታቀብ አሳሰቡ።

3. በአገራችን ውስጥ ያለውን የድህነት ችግር ለመቋቋም የሚረዳ የምግባረ ሠናይ ክፍል ለመመሥረት ተስማሙ።

4. በውስጥም ሆነ በውጭ ቤተክርስቲያናችንን የገጠሚትን ችግሮች ተቋቁሞ ለችግሮቹ መፍትሔ ለማግኘት እንዲቻል ጉባዔው ሰፋ ብሎ ምእመናንን እንዲያካትት ወሰኑ።

## ሁለተኛው ጉባዔ:-

በዋሽንግተን ዲሲ የተጀመረው ውይይት ስር እንዲሰድ እና አብዛኛው ምእመንም እንዲሳተፍበት፣ የቤተክርስቲያኑ የሰበካ ጉባዔ አባላት፣ የሽማግሌዎችና የእናቶች ተወካዮች፣ እንዲሁም የሰንበት ትምህርት ቤት አገልጋዮች ተሳታፊ የሆኑበት ጉባዔ ከ13 አብያተ ክርስቲያናት የተውጣጡ ካህናት፣ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያንና ዲያቆናት እንዲሁም ምሑራን በተገኙበት ከሚያዝያ 26 እስከ 27 ቀን 1999 ዓ.ም. በደብረ ሰላም መድኃኔዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንነ ሚኒያፖሊስነ ሚኔሶታ ተደረገ።

1. ይህ ጉባዔ በዋናነት ያስተላለፈው መልእክት «የቤተክርስቲያንን ሥርዓተ ቀኖናዋን የሚጋፉና አንድነቷን የሚፈታተን አፍራሽ ዝንባሌ ሲከሰት በዝምታ የሚመለከቱ የቤተክርስቲያን ልጆች አይኖሩም፤ በቤተ ክርስቲያኒቱ አንድነትና መሠረታዊ ህልውና ላይ ገለልተኝነት የሚባል ቋንቋ የለም። ሰዎች ሲወዱ ይዘውት የሚኖር ሲጠሉ ይዘውት የሚሰደድ ሲኖዶስ የለም። በመሆኑም ጠባብ አስተሳሰብን ሳንከተል ለቤተክርስቲያን መሠረታዊ አንድነትና ዘላቂ ሠላም በሚበጁ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ መወያየት እና የመፍትሔ መንገዶችን መፈለግ ክርስቲያናዊም ኢትዮጵያዊም ግዴታችን ነው። ነገር ግን ሲኖዶሱ አስተዳደራዊ ችግር እንዳለበት ግልጽ በመሆኑ እንዲሻሻሉና መልክ እንዲይዙ የሚገባቸው ነገሮች በቅደም ተከተል አጥኚ ኮሚነ ተመድቦላቸው ችግሮቹ ምን እንደሆኑና መፍትሄያቸውም ምን መምሰል እንደሚገባው ተጠንቶ በሲኖዶሱ አካባቢ የሚታዩት ደካማ ጎኖች ሁሉ በጋራ ጥረት ተስተካክለው መታየት አለባቸው። ይህ እስኪሆን ድረስ በገለልተኝነት እንቆያለን።» የሚል ነው።

2. ምግናረ ሠናይን በተመለከተ ጉዳዩን የሚያጠና አንድ ኮሚቴ፣ እንዲሁም በዚህ አገር ለተወለዱና ለሚወለዱ ኢትዮጵያውያን አንድ ወጥ የሆነ ሥርዓተ ትምህርት ለማዘጋጀት የሚወያይ ሌላ ኮሚቴ እንዲቋቋም ተወሰነ።

## ሶስተኛው ጉባዔ:-

በታምፓ ፍሎሪዳ አዲስ ዓለም ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከሐሙስ ኅዳር 19 እስከ ዓርብ ኅዳር 20/2000 ዓ.ም. በነበረው ስብሰባ ጉባዔው በሚከተሉት ርዕሶች ላይ ተወያይቶ ውሳኔዎች አሳልፏል።

1. በአገራችን በኢትዮጵያ በጅማና ኢሉባቦር አካባቢ በእምነታቸው ምክንያት በአክራሪ የእስልምና እምነት ተከታዮች አሰቃቂ ግፍና በደል ለደረሰባቸው፣ ከቤትና ንብረታቸው ለተፈናቀሉ ወገኖች መልሶ ማቋቋሚያ የገዳመ ተክለሃይማኖት የወገን ነፍስ አድን ድርጅት ባስጠናው ዕቅድ ላይ የሚውል የገንዘብ እርዳታ ለኢሉባቦር ፕሮጀክት እንዲላክ፤

2. የጉባዔው የመተዳደሪያ ደንብ ጸድቆ በሕግ ባለሙያዎች እንዲታይና ጉባዔውም ሕጋዊ አካል እንዲኖረው፤

3. የካህናትና የምዕመናን ጉባዔ መሠረታዊ ዓላማ እና ራዕይ ምን መምሰል እንዳለበት መግለጫ ወጥቷል።

ሶስቱም ጉባዔዎች በተካሄዱበት ወቅት ለውይይት እንዲረዱ በሊቃውንተ ቤተክርስቲያን አባቶች እና ምሁራን የተዘጋጁ ጥልቀት ያላቸው ጥናቶች ቀርበው ስብሰባዎቹ ሥርዓትን በተከተለ መንገድ ተከናውነዋል።

ከሶስቱ መደበኛ ስብሰባዎች ሌላ ጉባዔያችን በቴሌ-ኮንፈረንስ አገርና ቤተክርስቲያንን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት በማድረግ ርምጃዎችን ወስዷል። ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የሁለተኛው ጉባዔ ከተካሄደ በኋላ «ሲኖዶስ ተሰዷል» የሚለውን ወገን የሚወክሉ ግለሰቦች በድረ-ገጽ፣ በጽሑፍ እና በሬዲዮ አማካኝነት የገለልተኛ አብያተ ክርስቲያናትን ካህናትና የቦርድ አባሎች «ምንደኞችና የፖለቲካ ተጠሪዎች ናቸው» በማለት ሰፊ ስም ማጥፋት ዘመቻ ጀመሩ። ጉባዔያችንም ይህን ጥቃት በዝምታ ከማለፍ ይልቅ ምእመናንን ከተንኮለኞች ወጥመድ ማስጠንቀቅ አስፈላጊ መሆኑን በማመን በጽሑፍ መግለጫዎችን በመበተንና በራዲዮ ቃለ ምልልስ አማካኝነት ስም አጥፊዎችን ተቋቁሟል።

2. «የጥፋት ታሪክ እንዳይደገም» በሚል ርዕስ አንድ ቴሌ-ኮንፈረንስ ተጠርቶ በስብሰባው ላይ ተሳታፊ የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሐምሌ 24 ቀን 1527 ዓ.ም በደብረ ሊባኖስ ገዳም እና በሌሎች ቦታዎች በሰማዕትነት ሕይወታቸው ያለፈ ወገኖቻችንን በጸሎት እናስባቸዋለን። ለቀጣዩ የአገራችን ሕዝብ ሰላምና የመቻቻል ኑሮ ያለማቋረጥ እንጸልያለን ከማለት ባሻገር «ይህን የታሪክ አጋጣሚ በኀዘንና በጸሎት በምናስብበት ዕለት በአገራችን ኢትዮጵያ በጅማና ኢሉባቦር አደጋ የደረሰባቸውን፣ የግል መኖሪያ ቤቶቻቸውና አብያተ ክርስቲያኖቻቸው ፈርሰውና ተቃጥለውባቸው ከቦታቸውና ንብረታቸው ተፈናቅለው የሚገኙ ወገኖቻችንን በሚቻለን ሁሉ ለመርዳትና መልሶ ለማቋቋም ሐምሌ 24 ቀን 1999 ዓ.ም. በየአብያተ ክርስቲያናቱ የአንድ ሰንበት የሙዳይ ምጽዋት ገቢ ወይም የተለየ አስተዋጽኦ በመጠየቅ ለታሰበው የችግር ጊዜ የወገን ደራሽ ዕርዳታ ትብብር እናደርጋለን።» በማለት የተወሰነው ውሳኔ በታምፓ ፍሎሪዳ ከተካሄደው ስብሰባ በኋላ ተግባራዊ ሆኗል።

3. በኢትዮጵያ የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው በእስር እየተጉላሉ ለነበሩ እስረኞች ከእስር እንዲፈቱ መንግሥት አስቸኳይ እርምጃ እንዲወስድ ሲኖዶስ ይህን ጉዳይ በቸልተኝነት እንይመለከተው ሰፊ ደብዳቤ ተጽፎ ተልኳል። የደብዳቤውም ይዘት «ዛሬ ይህንን መልዕክት ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ስናቀርብና ስናስተላልፍ በቀራጥ ልጆቿ፣ በሃይማኖት አባቶቿ እና እናቶቿ ታፍራና ተከብራ የኖረችው ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ቀድሞ የነበራት አንድነት እየተዳከመ ደሃ ሲበደል እና ፍርድ ሲጓደል፣ ሰዎች በግፍ ሰንሰለት ታስረው በወህኒ ሲጋዙ፣ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ተከታዮች በአሰቃቂ ሞት ሲረግፉ፣ ፍትሕ ፈላጊዎች አለአግባብ ሲጨፈጨፉና በየቦታው ሲወድቁ እንደጥንታውያኑ የቤተክርስቲያን አባቶች ጥንካሬና እምነት በዚህ በያዝነው ዘመን በአገራችን እየተሠራ ያለውን አስከፊ ድርጊት ለመቃወም የቤተክስቲያን የሃይማኖት መሪዎች ድምጻቸውን ለመንግሥት ለማሰማት ለምን ሳይችሉ ቀሩ?» የሚል ነበር።

## <u>ማጠቃለያ፡-</u>

ጉባዔያችን ከተመሠረተ ጀምሮ ብዙ ተግባራትን ያከናወነ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ውጤታማ እንዳይሆን አንዳንድ ዋነኛ የሆኑ በውሳኔ የጸደቁ ጉዳዮችን ተግባራዊ ለማድረግ አልተቻለም። ከነዚህም ውስጥ ጎላ ብለው የሚታዩት የሚከተሉት ናቸው።

1. በሰሜን አሜሪካ በማደግ ላይ ላሉ ወጣቶች አንድ ወጥ የሆነ ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ሥራ አልተጀመረም።
2. ከገዳመ ተክለሃይማኖት የወገን ነፍስ አድን ድርጅት ጋር ጣምራ በመሆን በኢሉባቦር የተጀመረው መረባረብ በሌሎች በተጎዱ ቦታዎች አልቀጠለም።

3. በኢትዮጵያ ጥንታዊ ገዳማት የሚገኙትን የአብነት ትምህርት ቤቶች እና የቤተክርስቲያን ንዋየ ቅድሳትን ለመንከባከብ የገንዘብም ሆነ የዕውቀት ድጋፍ መስጠት አልተጀመረም።

ለነዚህ ሁሉ ጉድለቶች ዋና ምክንያቶች የሆኑት፡-

1. ጉባዔያችን ጥንካሬ እንዲኖረው ሕጋዊ አካል አለማግኘቱና ለሥራ ማስኬጃ በጀት ወጥቶ አባል የሆኑ አብያተክርስቲያናት ድርሻቸው ተወስኖ ገንዘብ መሰብሰብ አለመጀመሩ።

2. እያንዳንዱ ቤተክርስቲያን አካባቢው ባመቸው መንገድ በተናጠል በሚደረግ ጥረት የተገነባና ያደገ በመሆኑ በልዩ ልዩ ቤተክርስቲያናት በሚገኙ ምእመናን በኩል አንድ አይነት አመለካከትም ሆነ መግባባት ለማግኘት አዳጋች ሆኖ ይገኛል።

3. የአስተዳደር ቦርድ አባላት በየወቅቱ ስለሚቀያየሩ አዲስ ቡድን በመጣ ቁጥር ብዙ የጉባዔው ጉዳዮች እንደገና ጥሬ እየሆኑ ውሳኔዎችን በወቅቱ ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ ሆኗል። ባጠቃላይ ከራስ ቤተክርስቲያን አልፎ በሌሎች መተማመን እየጠፋ ብዙ የስብሰባ ጊዜ በሙግትና በጭቅጭቅ ይባክናል።

## የጉባዔያችን ራዕይ፡-

ዋናው አላማችን በአምላኛችን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተዋጀችውን፣ በነቢያትና በሐዋርያት መሠረትነት የታነጸችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን እምነት ሥርዓትና ትውፊት በመከተል፤ በመጠበቅና በማስጠበቅም ጭምር የልጅተት አደራችንን በመወጣት የእምነት አባቶቻችንን ትምሕርትና ቡራኬ፣ የወንድሞቻችን መምህራንን ስብከት፣ የሊቃውንተ ቤተክርስቲያንን ማኅሌት፣ የዘማርያኑን ዝማሬ በመቀበል «ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽማ የተሰጠች እምነትን» እየተከተልን በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን ማሳደግና አገራችንን እና ቤተክርስቲያንን ሳንዘነጋ በምንችለው ሁሉ በማገዝ የቤተክርስቲያናችን ድክመቶቿ ተወግደው፣ መንበሯ ጠንክሮ፣ አንድነቷን አጽንታ ስትገኝ ማየት ነው።

ይህንንም ራዕይ ተግባራዊ ለማድረግ፡-

1. በመጀመሪያ እንድንሰባሰብ አቢይ ምክንያት የሆነንን አካሄዳቸውን አበላሽተው በማን አለብኝነት «ሲኖዶስ በኢትዮጵያ ምድር የለም፤ እኛም ስንወጣ አብሮ ተሰዷል» ያሉት ወገኖች ኢቀኖናዊ ተግባር እንዳያንሰራራ አሁን ተዳክመዋል ብለን ሳንንቅ ምዕመናንን ከማስተማር እና ከማስጠንቀቅ ችላ እንዳንል ያስፈልጋል።

2. ፊታችንን ወደ አገራችን መለስ አድርገን ለቤተክርስቲያን ተቆርቋሪ ከሆኑ የቤተክርስቲያን አባቶች ጋር በመሆን በመወያየትና በመመካከር ቤተክርስቲያናችን ደካማ ጎኖቿን አስወግዳ ታሪካዊ ተልዕኮዋን እንድትወጣ አስፈላጊውን ሁሉ ጥረት ማድረግ ይገባል።

3. በወገናችን ላይ እየደረሰ ያለውን ጥቃት ለመቋቋም እንዲቻል አለንላችሁ በማለት አስፈላጊው እርዳታ እንዲደርስ የጀመርነው ምግባረ ሠናይ እንዲቀጥል ያስፈልጋል።

እነዚህን ሁሉ ድክመቶች ለማስወገድ ጉባዔያችንን አስፍተን ራዕያችንን ተግባራዊ እንድናደርግ እግዚአብሔር ይርዳን።